በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

በጤና ሚኒስቴር

የቅዱስ ጴጥሮስ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል

የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ

ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት /2015
አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

በጤና ሚኒስቴር

የቅዱስ ጴጥሮስ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል

የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የቅዱስ ጴጥሮስ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የተመደበለትን የመደበኛ እና የካፒታል በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የቅዱስ ጴጥሮስ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶች ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣

- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የቅዱስ ጴጥሮስ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በሆስፒታሉ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የሆስፒታሉ የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ማመዛዘኛ፣

ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የሆስፒታሉ የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ

የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት የመንግሥት ሠራተኞች የደመወዝ ክፍያ ከመፈጸሙ (ወጪ) ከመደረጉ በፊት መከናወን ካለባቸው ጥንቃቄዎች አንዱ በጡረታ ፣ በሞት እና በሌሎች ምክንያት ከስራ የተለዩ ሰራተኞች ከደመወዝ መክፈያ ዝርዝር መዉጣት እንዳለባቸዉ ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሰረት የሆስፒታሉ የ2015 በጀት አመት ሂሳብ ከስራ ለለቀቁ የሆስፒታሉ ሰራተኞች የተጣራ ደሞዝ በድምሩ ብር 33,170.706 ከመመሪያ ውጪ አላግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
2. የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8 /4 ፊደል መ የተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በመሆኑም በሆስፒታሉ በ2015 በጀት አመት በተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት ከተመለከተው ብር 2,518.21 ማስረጃው ያልቀረበለት ተሰብሳቢ ሂሳብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
3. የፌዴራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀፅ 8 በተራ ቁጥር 5 ላይ የተከፋይ ሂሳብ አያያዝን በተመለከተ በፊደል ሀ ላይ የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውም ወደፊት ክፍያ የሚፈፀምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸውን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብ መዝግበው መያዝ እንደሚችሉ ይገልፃል፡፡ በመሆኑም በሆስፒታሉ በ2015 በጀት አመት በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት ላይ ከታየው ብር 52,780.71 ማስረጃ ያልቀረበለት ተከፋይ ሂሳብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 3 በዝርዝር ከተገለጹት ሁኔታዎች በስተቀር የሆስፒታሉ የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት ትክክለኛውን ገጽታ ያሳያሉ፡፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

I. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች (Emphasise Matters)

1.1. የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 የመንግስት ሂሳብ አያያዝ ስርዓት ተ.ቁ 3 የሂሳብ አወቃቀር ስርአት በሚለው ስር የመንግስት መ/ቤቶች የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች በየመደባቸው ተለይተው መመዝገብ እንዳለባቸው መመሪያው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ሆስፒታሉ የተንቀሳቃሽ ስልክ ግዥ በ2311101 (6313) ቋሚ ዕቃዎች ግዥ መመዝገብ ሲገባው በ2231101 (243) ለፕላንትና ማሽነሪ ዕቃዎች ጥገና ብር 184,625.00 የመዘገበ በመሆኑ ወጪው በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ሳይመዘግብ ተገኝቷል፡፡

1.2. የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 የመንግስት የሒሳብ አያያዝ ዝርዝር አፈጻጸም ንዑስ ክፍል 8 የሒሳብ አያያዝ ዝርዝር አፈጻጸም ተ.ቁ 2ለ የወጪ ሂሳብ አያያዝ ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረብ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ሆስፒታሉ አመታዊ የሰራተኞች ስብሰባ ለማድረግ በዋጋ ማቅረቢያ አወዳድሮ አሸናፊ ከሆነው ከኤሊያና ሆቴል ጋር የመስተንግዶ አገልግሎት ለመጠቀም ለ300 ሰው የመስተንግዶ አገልግሎት በቀን 1,299.99 ብር ሂሳብ በ1 ሰው ለመክፍል ውል ገብቶ ሆቴሉ ለሰጠው የመስተንግዶ አገልግሎት በድምሩ ብር 389,996.97 (300 × 1,299.99) የከፈለ ሲሆን በስብሰባው ወቅት በቀረበ አቴንዳንስ መሰረት 203 ሰዎች ብቻ የፈረሙ ሲሆን 97 ሰዎች ስብሰባው ላይ ለመሳተፋቸው ሳይፈርሙ ሆስፒታሉ ብር 126,099.03 (97 × 1,299.99) ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

2. የህጋዊነት ጉዳዮች (Compliance Matters)

2.1 ሆስፒታሉ ከሲሉላር ትሬዲንግ ጋር የህክምና መሳሪያዎች እና መገልገያዎች ለመግዛት ውል ተዋውሎ በቀን 01/03/2015 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 9554 ብር 546,000.00 ክፍያ የፈጸመ ሲሆን በውሉ ላይ አቅራቢው አቅርቦቱን የሚጀምርበትና የሚያጠናቅቅበት ቀን ያልተጠቀሰ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

3 ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)

3.1 የንብረት አያያዝን በተመለከተ

የሆስፒታሉ ንብረትን አያያዝና አጠባበቅ በፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 የመንግስት ንብረት መጠበቂ ኦዲት ሲደረግ፤

i<u>በአላቂ ፣ በቋሚ እና በተሸከርካሪ መለዋወጫ ዕቃ ግምጃ ቤት የሚገኙ ዕቃዎችን በተመለከተ</u>

- በአላቂ ፣ በቋሚ እና በተሸከርካሪ መለዋወጫ ዕቃ ግምጃ ቤት የሚገኙ ዕቃዎችን በተመለከተ
- የ2015 በጀት አመት የቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፤
- የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ሞዴል 22 የሚዘጋጀው በዕቃ ግምጃ ቤት ባለሙያዎች ሲሆን የዕቃ ግምጃ ቤት ኃላፊነትም በነዚሁ ሠራኞች የሚከናወን መሆኑ፤
- በዕቃ ግምጃ ቤቱ ውስጥ ቋሚና አላቂ ዕቃዎች ፣ ያገለገሉ እና አዳዲስ ዕቃዎች ፣ መወገድ ያለባቸው ዕቃዎች በአንድ ላይ ተቀላቅለው የተቀመጡ መሆኑ፣
- በ2012 በጀት ዓመት ታትመው ገቢ የተደረጉ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኞች ብዛት ከ560 በላይ ፓዶች ወጪ ተደርገው ጥቅም ላይ ያልዋሉ መሆኑ፤
- በ2015 በጀት አመት በግዥ የገቡ እጅግ ብዛት ያላቸው የገላ ሳሙና ከ500 እስከ 1500 ዋት አቅም ያላቸው 57 ስታብላይዘሮች በግምጃ ቤቱ ውስጥ ያሉ መሆኑ፤

- ብዛት ያላቸው የተለያዩ የተሸከርካሪ የመለዋወጫ ዕቃዎችን የሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች ሆስፒታሉ የሉትም በሚል ከ8 አመት በላይ የተቀመጡ መሆኑ፤
- በ2014 በጀት አመት የገቡ 2 ፕሪንተሮች ያለአገልገሎት የተቀመጡ መሆኑ፤
- 12 ፓኬት ዱራታ ባትሪ ድንጋይ እና 2 የብረት ሳጥኖች ለረጅም አመታት የተቀመጡ መሆኑ፤
- ከጤና ሚኒስቴር በ2012 በጀት አመት በልገሳ የመጡ 15 አይፓዶች መስራት የማይችሉ ናቸው በሚል በግምጃ ቤቱ ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤
- በ2012 በጀት አመት ከቱላን ዩኒቨርስቲ በልገሳ የገቡ 76 ዴስክቶፕ ኮምፒዩተሮች ከነአክሰሰሪዎቻቸው ፣ 54 ስዊች ፓወር ኮኔክተር ፣ 8 ካርትሬጅ የፕሪንተር ቀለም ፤ 20 ካርቶን የኢንተርኔት ኬብል ፣ 1 ሲዲ ማተሚያ ማሽን ፣ 1 ቲቪ ኮንፈረንስ ፣ 4 ወልማውንት ካቢኔት አገልግሎት ላይ ሳይውሉ በግምጃ ቤቱ ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤

በውስጥ ኦዲት የስራ ክፍል አጠገብ በሚገኝ የዕቃ ግምጃ ቤት የሚገኙ ዕቃዎችን በተመለከተ

- በውስጥ ኦዲት ክፍል በር ፊት ለፊት 1 ማቀዝቀዣ (ፍሪጅ) በብልሽት ምክንያት ከ 1 አመት በላይ የተቀመጠ መሆኑ፤
- ለመደበኛ አገልግሎት ተገዝቶ ጥቅም ላይ ሳይውል የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቃ ከ2000 በላይ ባለ 250 ግራም ሰንሻይን የልብስ ማጠቢያ ሳሙናና ከ50 በላይ የዩፒኤስ ባትሪዎች የሚገኙ መሆኑ፤

<u>በተመላሽ የተሸከርካሪ መለዋወጫ ዕቃ ግምጃ ቤት የሚገኙ ዕቃዎችን በተመለከተ</u>

- በሆስፒታሉ ኮሚኒቲ ፋርማሲ ጀርባ ባለ ቦታ ላይ ከ50 በላይ የተለያዩ መጠን ያላቸው አሮጌ የተሽከርካሪ ጎማዎች ከ2014 ዓ.ም ጀምሮ ሳይወገዱ የተከማቹ መሆኑ፤

- ሳይካትሪ ዋርድ አካባቢ ባለ ክፍል ውስጥ ብዛት ያላቸው ተመላሽ የተሽከርካሪ መለዋወጫ ዕቃዎች ከ2 አመት በላይ ሳይወገዱ የተቀመጡ መሆኑ፤

- ብዛት ያላቸው ተመላሽ/አሮጌ/ የህክምና ዕቃዎች ከ10 አመት በላይ ሳይወገዱ የተቀመጡ መሆኑ፤

<u>በአላቂ የህክምና ቁሳቁሶች የዕቃ ግምጃ ቤት የሚገኙ ዕቃዎችን በተመለከተ</u>

- የዕቃ ግምጃ ቤት ጥበት በመኖሩ የህክምና ዕቃዎች ፣ የላብራቶሪ ሪኤጀንቶች በመድሀኒትና የህክምና ዕቃዎች አያያዝና አቀማመጥ እስታንዳርድ መሰረት ሳይሆን ተደራርበው የተቀመጡ መሆኑ፤

<u>የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቃ መድሀኒቶች እና አሮጌ የህክምና ዕቃዎች የተከማቹበት የዕቃ ግምጃ ቤትን በተመለከተ</u>

- የአገልግሎት ጊዜያቸው ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ ያበቃ እጅግ በጣም በርካታ የተለዩ መድሀኒቶች ፤ የላብራቶሪ ሪኤጀንቶች እና ሌሎችም የህክምና ቁሶች ሳይወገዱ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

- በግምጃ ቤቱ በር ፊት ለፊት ብዛት ያላቸው አሮጌ የህክምና አልጋዎች ፣ የህክምና ቁሳቁሶች፣ ወንበሮች እና ጠረጴዛዎች ሳይወገዱ የተቀመጡ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

3.2 ባለፉት በጀት ዓመታት የኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት በሆስፒታሉ እርምጃ ያልተወሰደባቸው፡-

<u>የ2014 በጀት አመት የኦዲት ግኝት</u>

- የኮቪድ 19 ልዩ አበል በአንድ ወር ውስጥ 2 ጊዜ ስማቸውን በማካተት ለዶ/ር ትነበብ ስዩም ብር 30,400.00 በግሮስ ተሰርቶ የተጣራ ብር 22,425.00 የተከፈላቸው ሲሆን በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ብር 19,469.50 ወደ መንግስት አካውንት ተመላሽ ያደረጉ ሲሆን ቀሪ ብር 2,955.50 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፡፡

- የኮቪድ 19 ልዩ አበል በአንድ ወር ውስጥ 2 ጊዜ ስማቸውን በማካተት ለዶ/ር ፍቅርተ ወልዴ ብር 10,500.00 የተከፈላቸው ሲሆን በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፡፡
- 7 መኪናዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌላ መ/ቤቶች ስም ተመዝግበው የሚገኙ ሲሆን በሆስፒታሉ ስም የባለቤትነት ደብተር እንዲወጣላቸው የኦዲት አስተያየት የተሰጠ ሲሆን እስካሁን ያልወጣላቸው መሆኑ፡፡
- በሆስፒታሉ አስተዳደር ቢሮ ውስጥ 1 (HONDA) ሞተር ሳይክል ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ታርጋ ሳይወጣለት እና አገልግሎት ሳይሰጥ ቆሞ የሚገኝ ሲሆን ታርጋ ወጥቶለት አገልግሎት እንዲሰጥ በኦዲት አስተያየት የተሰጠ ሲሆን እስከ አሁን ያልተተገበረ መሆኑ፡፡ እንዲሁም 1 ባጃጅ አምቡላንስ ታርጋ ያልወጣለት ሲሆን ታርጋ ወጥቶለት አገልግሎት እንዲሰጥ በኦዲት አስተያየት የተሰጠ ሲሆን ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፡፡

<u>የ2013 በጀት ዓመት ግኝቶች</u>

- የሆስፒታሉ ሰራተኞች ከመደበኛ ሥራቸው ከለቀቁ በኋላ የተፈጸመ የደመወዝ ክፍያ በድምሩ ብር **26,142.98** ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- ሰራተኞች በዓመት እረፍት እና በወሊድ ፍቃድ ላይ እያሉ የኮቪድ-19 የማበረታቻ ልዩ አበል ክፍያ ብር 8,882.50፤ እና በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በተመሳሳይ ቀናት ሁለት ጊዜ የኮቪድ-19 የማበረታቻ ልዩ አበል ክፍያ ብር 19,075.00፤ በጠቅላላው ብር **27,957.50** የተከፈለው ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
- የኮቪድ 19 የማበረታቻ ልዩ አበል ክፍያ የሥራ ግብሩ ከደመወዝ ጋር ተደምሮ ባለመሰራቱ ምክንያት ብር 1,172,364.39 ወደ መንግስት አካውንት ተመላሽ እንዲደረግ በኦዲት አስተያየት ከተሰጠው ውስጥ ብር **679,330.70** ከየካቲት 2015 ዓ.ም እስከ ህዳር 2016 ዓ.ም ድረስ ገቢ የሆነ ሲሆን ቀሪው ብር **493,033.66**ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፡፡
- በኃላፊነት ተመድበው ይሰሩ የነበሩ ሰራተኞች በተለያዩ ጊዜ ወጪ ያደረጉትን በጠቅላላው ብር **28,272.78** ዋጋ ያለው ሁለት ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮችን ከሥራ ሲለቁ ተመላሽ ያላደረጉ መሆኑ፤

የ2008 በጀት ዓመት

- ታይም ኢንጂነሪንግ ከሆስፒታሉ ጋር ባደረገው የኤሌክትሪክ ፍጆታ ወጪ የመጋራት ውል ስምምነት መሠረት ከሚፈለገው ብር 32,883.93 ወስጥ ብር 6,457.44 ተመላሽ ያደረገ ሲሆን ቀሪውን ብር **26,426.49** ተመላሽ ያላደረገ መሆኑ፤

2007 በጀት ዓመት

- ሚሊቭ ኮንስትራክሽን ከሆስፒታሉ ጋር ባደረጉት የኤሌክትሪክ ፍጆታ የወጪ የመጋራት ውል ሥምምነት መሰረት የሚፈለግበትን ብር **8,783.16** ተመላሽ ያላደረገ መሆኑ፤

2005 በጀት ዓመት

- በ2005 በጀት ዓመት ያለአግባብ የተከፈለው ውሎ አበል **1,375.25** ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት

መጋቢት/ 2016